# ተደጋግሞ የሚነሱ ጥያቄዎች

### ወደ ቡድንዎ ሪፈራል እንዴት አደርጋለሁ?

የሚያስፈልገን የሚከተሉትን ጠቅሰው ኢሜል ወይም የድምጽ መልእክት ብቻ ነው፡-

- የነዋሪው ስም እና የትውልድ ቀን።
- የተቋሙ ስም እና እዛ ያለ ሰው ኢሜይል/ስልክ ቁጥር።
- የባህሪ ተግዳሮት አጭር መግለጫ።
- ተቋሙን ወክለው ሪፈር የሚያደርጉ ከሆነ፣ ሪፈራል ስለማድረግ እንደተናገሩ እና እኛ እንድንደውልልዎ መስማማትዎን እንዲነግሩን እንፈልጋለን።

### ለነዋሪዎች የአእምሮ ጤና ምክር ይሰጣሉ?

አይ፣ ይህ ከቡድናችን ወሰን ውጪ ነው። እኛ የምንሰራው ከተቋማት ጋር ነው- ከነዋሪዎች ጋር አይደለም። ነገር ግን፣ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች የሚያስፈልጉ ከሆነ፣ ያንን ፍላጎት ለማሟላት የአካባቢ መርጃዎችን እንዲያገኙ ልናግዝዎ ደስተኞች ነን።

### ነዋሪው Medicaid ሊኖረው ይገባል ወይስ እርስዎ እንዲያግዙ ተቋሙ Medicaid መቀበል አለበት?

አይደለም! ተቋሙ የነርሲንግ ቤት፣ የታገዘ የመኖሪያ ተቋም፣ የአዋቂ ቤተሰብ ቤት ወይም የሚደገፍ የመኖሪያ ቤት በRCS ፈቃድ ያለው ወይም የተረጋገጠ ከሆነ፣ ሪፈራል እንቀበላለን!

### ያቀረቡት መረጃ 'ጥቅስ-ማስረጃ' መሆኑ የተረጋገጠ ነው?

እያንዳንዱ ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በጣም ብዙ ምክንያቶች ስላሉ ይህንን ዋስትና መስጠት አንችልም። ነገር ግን፣ የምንሰጠው መረጃ ከደንቦቹ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለማረጋገጥ ጠንክረን እንሰራለን። ይህ እንደ አስፈላጊነቱ ከ RCS ፖሊሲ ሰራተኞች እና ከሌሎች የርእሰ ጉዳይ ባለሙያዎች ጋር መስራትን ይጨምራል።



## ለበለጠ መረጃ ወይም ሪፈራል ለማድረግ፣ በሚከተለው ያግኙን፡-


**RCSBHST@dshs.wa.gov**
(አጠቃላይ ጥያቄዎች)

**ALTSABHSTTRAINING@dshs.wa.gov**
(የሥልጠና ጥያቄዎች)

**360-725-3445**

**ድረ-ገፅ**
የሚከተለሉትን ለመማግኘት የQR ኮድን ይቃኙ

Residential Care Services
P.O. Box 45600
Olympia, WA 98504-5600


### አቅራቢዎች ምን ይላሉ፡-

"[አማካሪው] ጭንቀቴን ሰምቶ ጥሩ ሐሳቦች አብራርቶልኛል።"

"ከነዋሪው ጋር እያጋጠሙን ያሉ ጉዳዮችን በተመለከተ ሀሳቤ የተደመጠ መስሎኛል።"

"ድጋፍ ሁል ጊዜ እንዳለ እና ስልክ መደወል ብቻ እንደሚያስፈልገኝ አውቃለሁ።"


የማህበራዊ እና ጤና አገልግሎት መምሪያ
የአረጋዊያን እና የረዥም ጊዜ ድጋፍ አስተዳደር
Residential Care Services


# የባህሪይ ጤና ድጋፍ ቡድን



# የረጅም ጊዜ እንክብካቤ አቅራቢዎች አገልግሎት


Washington State Department of Social & Health Services
Transforming lives

DSHS 22-1940 AM (7/23) Amharic

# ስለ BHST

ህይወቶችን መቀየር እና ለባህሪይ ጤና የቀረቡ ማህበረሰብ-ተኮር አገልግሎቶችን መጨመር የ Washington ግዛት ጥረት አካል ስለሆነ የነዋሪዎች እንክብካቤ አገልግሎት የባህሪይ ጤና ድጋፍ ቡድን ፈጥሯል፡፡

የ RCS BHST ዋና ግብ የረጅም ጊዜ እና ማህበረሰብን መሰረት ባደረጉ አካባቢዎች ለሚኖሩ የባህሪ ተግዳሮቶች ላላቸው ሰዎች የረጅም ጊዜ ስኬት ነው። ይህንን ለማሳካት፣ BHST የተቋሙ ሰራተኞች ከፍተኛ ጥራት ያለው፣ ሰውን ያማከለ እንክብካቤን ደንቦችን በማክበር እንዲረዱ፟ቸው ክሊኒካዊ እና የቁጥጥር እውቀትን ይሰጣል።

የእኛ የፈቃደኝነት፣ ምንም ወጪ የማይጠይቁ አገልግሎቶቻችን በክልል ደረጃ ይገኛሉ። እኛ የRCS አካል ብንሆንም፣ ቅሬታ መርማሪዎች፣ ቀያሾች ወይም ፍቃድ ሰጪዎች አይደለንም።




# የእኛ አገልግሎቶች



### ምክክር

ለአቅራቢዎች ፈታኝ የሆነን ነዋሪ የሚንከባከቡበት አዳዲስ መንገዶችን ለመስጠት የባህሪ ጤናን እና የቁጥጥር እውቀትን የሚያዋህድ ነዋሪ-ተኮር ምክክር።

### የመጀመሪያ ደረጃ የቴክኒክ ድጋፍ

የታወቀ የአስቸጋሪ ባህሪያት ታሪክ ያለው ግለሰብን ለመቀበል ሲዘጋጁ አቅራቢዎች ስለ ደንቦች እና ጣልቃገብነቶች ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ለመርዳት የታሰበ የምክክር አይነት ነው።



### ስልጠና

የBHST ማሰልጠኛ ስፔሻሊስት ልዩ የሆነ የባህሪ ጤና እና የቁጥጥር እውቀት ድብልቅ አለው። በእያንዳንዱ የ1-2 ሰአታት ስልጠና፣ WACsን በማክበር ለተለያዩ ፈታኝ ባህሪያት ውጤታማ ምላሽ ለመስጠት ቴክኒኮችን እና ስልቶችን ይማራሉ።

### የግንኙነት ካፌ

በአንድ የተወሰነ ነዋሪ ላይ ያላተኮረ መደበኛ ያልሆነ ከአማካሪ ጋር የሚደረግ የጥያቄ እና መልስ። ስለ ባህሪ ተግዳሮቶች፣ የእንክብካቤ እቅድ፣ WACs እና ወደ አእምሮዎ የሚመጣውን ማንኛውንም ነገር ይጠይቁን!



### የጠበቁትን አላገኙም?

ተለዋዋጭ ለሆነው የአቅራቢዎች ፍላጎት ምላሽ አልፎ አልፎ አዳዲስ አገልግሎቶችን እንጨምራለን። ኢሜል ይላኩልን እና ለእርስዎ ሁኔታ የተሻለውን መፍትሄ ለመወሰን ከእርስዎ ጋር እንሰራለን።

# ከቡድኑ ጋር ይገናኙ

አሰልጣኞቻችን እና አማካሪዎቻችን ፈቃድ ያላቸው ማህበራዊ ሰራተኞችን፣ ፈቃድ ያላቸው የአእምሮ ጤና አማካሪዎችን እና ሌሎችንም ያጠቃልላሉ - በ Western State ሆስፒታል፣ በ McNeil Island ልዩ ቃል ኪዳን ማእከል፣ የማህበረሰብ የአእምሮ ጤና ኤጀንሲዎች፣ የቤት እና የማህበረሰብ አገልግሎቶች፣ የአካባቢ ፍርድ ቤቶች እና የባህርይ ጤና ቀውስ ክፍሎች የመስራት ልምድ አላቸው።

## አማካሪዎች



Melissa Thomas፣ MS፣ LMHCA
melissa.thomas@dshs.wa.gov



Jean Horton፣ LMHC፣ GMHS
jeannette.horton@dshs.wa.gov



Julie Olivier
julie.olivier1@dshs.wa.gov



Valerie Turrentine፣ MPA
valerie.turrentine@dshs.wa.gov



Andy Cochran
andrew.cochran@dshs.wa.gov



Nicole Moon
nicole.moon@dshs.wa.gov

## የክፍል አስተዳዳሪ



Alixandria Cortez፣ MAP
alixandria.cortez@dshs.wa.gov

## አሰልጣኝ



Krystle Malo